*የሰበር መ/ቁ. 16301*

*ኅዳር 2 ቀን 1998 ዓ.ም*

*ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ*

*አቶ ሐጐስ ወልዱ*

*አቶ ተገኔ ጌታነህ*

*አቶ ዳኜ መላኩ*

*ወ/ሮ ደስታ ገብሩ*

*አመልካች፡- ተገኝ እንግዳ*

*ተጠሪ፡- አስናቀች ኪዳኔ*

*የመጥሪያን አደራረስ አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተናገድበት ሁኔታ - በሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት ተከሳሽ በሌለበት ክስ እንዲታይ የሚደረግበት ሁኔታ - የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 103፣ 105(1)*

አመልካች እሱ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲታገድለትና እሱም ወደ ክርክሩ እንዲገባ እንዲፈቀድለት የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን የጠየቀ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አመልካች የሥነ-ሥርዓት ሕጉ በደነገገው መሠረት ተጣርቶ ባለመቅረቡ ክርክሩ እሱ በሌለበት መታየቱ ባግባቡ ነው ሲል በመወሠን ጥያቄውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተመሣሣይ ውሣኔ በመስጠቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡

__ውሳኔ__፡- የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያፀናው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

1. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 103 እንደተመለከተው መጥሪያ አድራሽ (ሰጪው) መጥሪያውን ለማድረስ ያልቻለበትን ምክንያት በቃለ መሐላ አረጋግጦ መጥሪያውን ለፍርድ ቤቱ ይመልሳል፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበለትን ምክንያት እንደየሁኔታው በመመዘን ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
2. ፍርድ ቤቱ መጥሪያው እንደተመለሠለት በሕጉ በተመለከተው መሠረት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ምትክ የመጥሪያ አደራረስ ስርአት ማስተላለፉ ሕጋዊ ውጤት ያለው ይሆናል፡፡





ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ሐጐስ ወልዱ

አቶ ተገኔ ጌታነህ

አቶ ዳኜ መላኩ

ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

አመልካች፡- ተገኝ እንግዳ - ቀረበ

ተጠሪ፡- አስናቀች ኪዳኔ - አልቀረበችም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

__ፍ ር ድ__

አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገው የመጥሪያን አደራረስ በተመለከተ የተነሣውን ቅሬታ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረችው የአሁኗዋ ተጠሪ ናት፡፡ አመልካቹ በተደረገለት ጥሪ መሠረት አልቀረበም ስለተባለ ክርክሩ እሱ በሌለበት ታይቶ መወሰኑን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ በኋላ መዝገቡ የተንቀሣቀሰው አመልካች እሱ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሣኔ እንዲታገድለትና እሱም ወደክርክሩ እንዲገባ እንዲፈቀድለት በመጠየቁ ነው፡፡ ጥያቄው የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ፣ ተከሣሽ የስነ - ሥርዓት ሕጉ በደነገገው መሠረት ተጣርቶ ባለመቅረቡ ነው ክርክሩ እሱ በሌለበት እንዲታይ የተደረገው፡፡ የሚል ምክንያት በመስጠት ሣይቀበለው ቀርቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተመሣሣይ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ማለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 859 ሚያዝያ 5 ቀን 96 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው፡፡

ክሱ አመለካች በሌለበት እንዲታይ የተደረገው መጀመሪያ በቀጥታ በአድራሻው በመቀጠልም በጋዜጣ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ሊቀርብ አልቻለም በሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ መጀመሪያ በቀጥታ በአድራሻው የተላከለትን መጥሪያ ሊገኝ ባለመቻሉ መስጠት እንዳልተቻለና ወኪሉም መጥሪያውን አልቀበልም ስለማለቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 103 መሠረት በመሐላ ተረጋግጦ ለፍ/ቤቱ በመቅረቡ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 105(1) መሠረት የጋዜጣ ጥሪ እንዲተላለፍ ማዘዙንም ተመልክተናል፡፡ አመልካች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ትእዛዝ ተሰጡብኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ያቀረበው እነዚህን የሥነ - ሥርዓት ደንቦች በመከተል የተከናወነው ሂደት ትክክል አይደለም፡፡ መጥሪያው በደንብ እንዲደርሰኝ ሣይደረግ ነው ክርክሩ በሌለሁበት እንዲታይ የተደረገው፡፡ መጥሪያው መጥቶልኝ አልቀበልም አላልኩም፡፡ ስራዬ ሾፌርነት በመሆኑም ጋዜጣውን ማየት ይችላል ተብሎ መገመት የለበትም በማለት ነው፡፡

ከፍ ሲል ከተመለከቱት ሁኔታዎች ማየት እንደሚቻለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.94(1) በተደነገገው መሠረት መጥሪያውን ለአመልካቹ ልኮአል፡፡ ሆኖም አመልካቹ በአድራሻው ተፈልጎ ባለመገኘቱ እና ሌላም መጥሪያውን መቀበል የሚችል ሰው ሊገኝ ባለመቻሉ በታቀደው ሁኔታ መጥሪያውን ማድረስ ሳይቻል ቀርቶአል፡፡ ይህን መሰል ችግር ሲያጋጥም የሥነ ሥርዓት ሕጉ መፍትሄ አስቀምጦአል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 103 እንደተመለከተው መጥሪያ አድራሹ (ሰጭው) መጥሪያውን ለማድረስ ያልቻለበትን ምክንያት በመሐላ ቃል አረጋግጦ መጥሪያውን ለፍ/ቤቱ ይመልሳል፡፡ ፍ/ቤቱም የቀረበለትን ምክንያት እንደየሁኔታው በመመዘን ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ ይህም ማለት ተከሣሽ መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ ያለመሆኑ ወይም ደረሰኝ ለመስጠት እምቢተኛነቱ በመሐላ በተሰጠ ቃል ከተረጋገጠለት መጥሪያው በትክክል እንደደረሰ በመቁጠር ክርክሩ ተከሣሹ በሌለበት እንዲታይ ያደርጋል፡፡ መጥሪያው በትክክል እንደደረሰ ለመቁጠር የሚያስችል ምክንያት ካላገኘ፤ ነገር ግን የመጀመሪያው ሙከራ ተደርጎ ተቀባይ ባለመገኘቱ ምክንያት መጥሪያው መመለሱን ካመነ ደግሞ ቀጥሎ ያለውን ሌላው የመጥሪያ አሰጣጥ ሥርዓት (አማራጭ) ይጠቀማል፡፡ ይህ አማራጭም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.105 ከተመለከቱት አንዱ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መጥሪያው እንደተመለሰለት ወዲያውኑ አመልካች በሌለበት ክርክሩ እንዲታይ አላዘዘም፡፡ ተገቢ ሆኖ ያገኘው አካሄድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 105(1) ከተመለከቱት ከምትክ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓቶች አንዱን ማለትም የጋዜጣ ጥሪ ማስተላለፍ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተገቢ ነው ያለውን አማራጭ የመወሰን ሥልጣንም የፍ/ቤቱ ነው፡፡ በጋዜጣ የሚደረግ ጥሪ በሕጉ ከተፈቀዱት ምትክ የመጥሪያ አሰጣጥ ሥርዓቶች አንዱ በመሆኑም ሕጋዊ ውጤት ያለው ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች በመጨረሻ ያቀረበውን ጥያቄ ያልተቀበሉትም በዚህ ምክንያት እና ጥሪው የተላለፈው ተገቢውን የሥርዓት ደንብ ተከትሎ መሆኑን በማረጋገጣቸው ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የፈፀሙት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የሥር ፍ/ቤቶች ትእዛዞች ፀንተዋል፡፡
2. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡



የመ/ቁ. 10797

ታህሣሥ 27 ቀን 1998 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ አሰግድ ጋሻው
4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ

መልስ ሰጭዎች፡- 1. ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም
2. አቶ ሁሴን አብደላ
3. አቶ ንጉሴ ኃይሉ

*ስለ ወንጀል የተወሰነ ቅጣት-የገንዘብ ቅጣቶች - ወንጀሉ የሚያስከትላቸው ሌሎች የገንዘብ ውጤቶች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 99 - ስለፍርድ አፈፃፀም - የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 378*

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 1/89 መ/ሰጭዎች ለአመልካች 16,000,000 /አሥራ ስድስት ሚሊዮን/ የአሜሪካ ዶላር እንዲከፍሉ የሰጠውን ውሣኔ ለማስፈጸም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 መሠረት ያቀረበውን ማመልከቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 መሠረት ሊፈጸም የሚችል ፍርድ የለም ለማለት ፍ/ቤቱ በአብላጫ ድምፅ ውድቅ በማድረጉ የቀረበ አቤቱታ፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>፡-የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳይ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ እንጅ ባለሀብቱ የፍትሐብሔር ክስ አላቀረበም ወይም ፍርድ ያገኘበት ውሣኔ ለአፈፃፀም የሚያበቃ የፍትሐብሔር ፍርድ አይደለም ተብሎ ሊከለከል የሚችል አይደለም፡፡
2. ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳይ በፍርድ የተወሰነውን ገንዘብ የውሣኔው ባለመብት ሌላ ቀጥታ የፍትሐብሔር ክስ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ ሊፈጽም የሚችል ፍርድ ነው፡፡